# በማዕድን ሥራዎች ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ፈቃድ ለሚጠይቁ አመልካቾች የወጣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ

## ቁጥር 277/2013 ዓ.ም

RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

# በማዕድን ሥራዎች ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ፈቃድ ለሚፈልጉ አመልካቾች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት መመሪያ

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ « በማዕድን ሥራዎች ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ፈቃድ ለሚጠይቁ አመልካቾች የወጣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 277/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ :-

2.1. « ገምጋሚው አካል » ማለት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስትር ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የወከለው መምሪያ ነው::

2.1. « ማዕድን » እና « የማዕድን ሥራዎች » ማለት በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይኖራቸዋል::

2.1. « ማማከር » ማለት የማዕድን ሥራዎችን በብቃት በመረዳት ስለሥራው ወይም ከሥራው ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች ሙያዊ እገዛ፣ ምክር እና/ አስተያየት መስጠት ነው::

2.4. « ድርጅት » ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ክፍል ሁለት
## የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማስረጃ የሚሰጥባቸው ዘርፎች

3. የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማስረጃ ሊሰጥባቸው የሚችሉ የማዕድን ሥራ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው::

3.1. በማንኛውም ማዕድን የፍለጋ ሥራ፣

3.2. በማንኛውም ማዕድን የምርመራ ሥራ፣ የፕሪፊዚቢሊቲ እና የፊዚቢሊቲ ጥናቶች፣

3.3. በማንኛውም ማዕድን የማምረት ሥራ፣

3.3.1 ባህላዊ ማዕድን የማምረት ሥራ፣
3.3.2 አነስተኛ ደረጃ የማዕድን የማምረት ሥራ፣
3.3.3 ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን የማምረት ሥራ፣

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

3.4. ከማዕድን ሥራዎች ጋር ተዛማጅነት ባላቸው በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣አጠባበቅ እና ማኔጅመንት (Natural Resource Utilization, Protaction and Management ) ናቸው::

4. በተጨማሪም በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱና ገምጋሚው አካል አግባብነቱን በማየት የሚያስተናግዳቸው ከማዕድን ሥራዎች ጋር የተያየዙ ወይም ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ተግባራት ሊኖሩ ይችላሉ::

## ክፍል ሦስት
## ማመልከቻ

5. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማመልከቻ በግለሰብ ወይም በድርጅት ስም መቅረብ የሚችል ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት:-

5.1 አመልካቹ የተፈጥሮ ሰው ከሆነ:-

5.1.1. ሙሉ ስም፣ጾታ፣

5.1.2. የትውልድ ቀንና ቦታ፣

5.1.3. ዜግነት፣የመታወቂያ (ፓስፖርት) ቁጥር፣

5.1.4. የሥራና የመኖሪያ አድራሻ፣

5.1.5. የትምህርት ማስረጃዎች ቅጂዎች፣

5.1.6. የሙያ ብቃት ማስረጃው የሚጠየቅበት (ባቸው) የማማከር አገልግሎት ሥራ ዘርፍ(ፎች)፣

5.1.7. የሥራ ልምድ መግለጫ እና ይህንኑ የሚያረጋግጥ አመልካቹ ከሠራበት(ባቸው) መ/ቤት (መ/ቤቶች) የተሰጠ ማስረጃ፣

5.1.8. አመልካቹ በመንግሥት ሥራ ላይ አለመሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፣

5.2. አመልካቹ ድርጅት ከሆነ:-

5.2.1. የአመልካቹ ስም፣ዜግነቱና የሕግ አቋም፣

5.2.2. በአግባቡ የተረጋገጠ የድርጅቱ የመመሥረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂዎች፣

5.2.3. የድርጅቱ ሙሉ አድራሻ

5.2.4. ድርጅቱ የሙያ ብቃት ማስረጃውን በጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ ቀጥሮ ስለሚያሠራቸው ባለሙያዎች ዝርዝር መረጃ (ስም፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የሥራ ልምድ መግለጫ፣ የሙያ ዓይነት)::



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ባለሙያው ከሠራበት (ባቸው) መሥሪያ ቤት (ቤቶች) የተሰጠ የሥራ ልምዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረብ አለበት::

5.2.5. ድርጅቱ የሙያ ብቃት ማስረጃውን በጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ ቀጥሮ ከሚያሠራቸው ባለሙያዎች ጋር የተደረገ የውል ሰነድ ቅጂ፣

5.2.6. የሙያ ብቃት ማስረጃ ጥያቄው በቀረበበት የማማከር አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች እና የሥራ ኃላፊዎች በሙሉ በመንግሥት ሥራ ላይ ያልተሰማሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

5.2.7. የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማስረጃ የተጠየቀበት (ባቸው) የማዕድን የሥራ ዘርፍ (ፎች)፣

5.2.8. የማማከር አገልግሎት ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ባለሙያ ማንነት እና የዚሁ ባለሙያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.4፣ 2.5 እና 2.6 የተገለጹ ሰነዶችን፣

5.2.9. የማማከር አገልግሎት ሥራውን በኃላፊነት የሚመራው ግለሰብ የሙያ ብቃት ማስረጃው በተጠየቀበት ዘርፍ ወይም ከአንድ በላይ ከሆነ ቢያንስ በአንዱ ዘርፍ በዚህ መመሪያ መሠረት ለማማከር አገልግሎት ብቁ የሆነ ባለሙያ መሆን አለበት::

5.2.10. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ም/ሥራ አስኪያጅ የሙያ ብቃት ማስረጃው በተጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ ወይም ዘርፎች ቢያንስ በአንዱ ተመሳሳይ ሙያ ሊኖረው ይመረጣል::

5.3. አንድ አመልካች ግለሰብ በሚያቀርባቸው የሙያ ስልጠና ማስረጃዎች መሠረት እንዲሁም አንድ ድርጅትም በሚያቀፋቸው ባለሙያዎች የተለያየ የሙያ ስብጥር መሠረት ከአንድ በላይ በሆኑ የማማከር አገልግሎት ዘርፎች ላይ ለመሳተፍ ሊያመለክት ይችላል::

## ክፍል አራት
## የሙያ ዘርፎች

6. በግልም ሆነ በድርጅት የቀረቡት ባለሙያዎች በማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት ቀጥለው በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች በአንዱ የትምህርት ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል::

6.1. በጂኦሎጂ፣
6.2. በጂኦፊዚክስ፣
6.3. በጂኦኬሚስትሪ፣
6.4. በኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ፣
6.5. በኢኮኖሚክ ጂኦሎጂ፣
6.6. ሃይድሮጂኦሎጂ፣
6.7. በስትራክቸራል ጂኦሎጂ፣
6.8. በማይኒንግ ኢንጂነሪንግ፣
6.9. በማይኒንግ ጂኦሎጂ፣
6.10. በሚኒራሎጂ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር መዝገብ ቤት RECORD Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

6.11. በሚኒራል ኢኮኖሚክስ፣

6.12. እንዲሁም ገምጋሚው አካል የሙያ ብቃት ማስረጃው ለተጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ አግባብ መሆናቸውን አገናዝቦ የሚቀበላቸው ሌሎች ማዕድን ነክ የሙያ ዘርፎች::

## ክፍል አምስት
## የመገምገሚያ መሥፈርቶች

### 7. የትምህርት ደረጃ

የሙያ ብቃት ማስረጃው በተጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተገለጹት የሙያ ዘርፎች ቢያንስ በአንዱ ትምህርታቸውን በባችለር ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ደረጃ ያጠናቀቁ መሆን አለባቸው::

### 8. የሥራ ልምድ

የሙያ ብቃት ማስረጃው በተጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ቢያንስ በአንዱ የትምህርት መስክ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 በተገለጸው ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት በመስክም ሆነ በቢሮ በማዕድን ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ቢያንስ የአሥር (10) ዓመት አገልግሎት በዘርፉ ሊኖራቸው ይገባል::

9. በግል የቀረበ አመልካች የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት ተገቢውን የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል::

10. አመልካቹ ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ የሚያቀርባቸው ባለሙያዎች እያንዳንዳቸው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 መሠረት ተገቢውን የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል:: የድርጅቱ የሙያ ብቃትም መሥፈርቶቹን በሚያሟሉ በእነዚሁ ባለሙያዎች ላይ በመመርኮዝ ይወሰናል::

11. በግልም ሆነ በድርጅት የቀረበ ባለሙያ የሙያ ብቃት የሚገመገመው የባለሙያው የትምህርት ዘርፍ እና የሥራ ልምድ የሙያ ብቃት ማስረጃው ለተጠየቀበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ (ዘርፎች) አግባብ ያለው መሆኑን በማገናዘብ ይሆናል::

## ክፍል ስድስት
## የገምጋሚው አካል ተግባር

12. ገምጋሚው አካል በግልም ሆነ በድርጅት የቀረቡትን ባለሙያዎች የሙያ ብቃት በዚህ መመሪያ መሠረት ይገመግማል::

13. አመልካቹ ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ ከሚያቀርባቸው ባለሙያዎች መካከል በዚህ መመሪያ መሠረት በማዕድን ሥራዎች የማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት ተገቢውን የሙያ ብቃት የሌለው ባለሙያ ካለ ገምጋሚው አካል እንዲህ ዓይነቱን ባለሙያ ሰርዞ በዚህ መመሪያ መሠረት ብቁ በሆኑ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ባለሙያዎች ላይ በመመርኮዝ የድርጅቱን የሙያ ብቃት ይወስናል:: እንዲህም ሲያደርግ ድርጅቱ ይህንኑ እንዲያውቀው ያደርጋል::

14. ገምጋሚው አካል በመመሪያው መሠረት ተሟልተው የቀረቡለትን የግለሰቡን ወይም የድርጅቱን ሰነዶች በዚህ መመሪያ በቀረቡት የሙያ የብቃት መገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት ከገመገመ በኋላ ብቁ ሆነው ለተገኙት አመልካቾች ብቁ በሆኑባቸው ዘርፎች የሙያ ብቃት ማስረጃ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ ለበላይ ኃላፊው ያቀርባል:: ሲፈቀድም የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀቱን ይሰጣል::

15. ገምጋሚው አካል የማምገማውን መስፈርት አሟልተው ያልተገኙ አመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደርጋል:: ይህንን ሲያደርግም ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት የሚገልጽ ደብዳቤ ለአመልካቹ እንዲደርስ ያደርጋል::

## ክፍል ሰባት
## የምስክር ወረቀት

16. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለበት::

16.1. የአመልካች ስም፣
16.2. ዜግነት፣
16.3. የአመልካቹ የሥራ አድራሻ፣
16.4. የምስክር ወረቀት የተሰጠበት ቀንና ዓመተ ምህረት፣
16.5. የማማከር አገልግሎት የሚሰጥበት ዘርፍ(ፎች)፣
16.6. የምስክር ወረቀቱ የዕድሳት ዘመን፣
16.7. የምስክር ወረቀት የሰጠው የሥራ ኃላፊ ስምና ፊርማ፣
16.8. የምስክር ወረቀት የሰጠው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማህተም፣

## ክፍል ስምንት
## ዕድሳት

17. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል::

18. አመልካቾች ዕድሳቱ እንዲፈጸምላቸው የሙያ ብቃት ማስረጃው ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ከማብቃቱ ከሠላሣ (30) ቀናት በፊት ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: ገምጋሚው አካልም ማመልከቻው በደረሰው በሠላሣ (30) ቀናት ውስጥ መርምሮ እድሳቱን ይፈጽማል::

## ክፍል ዘጠኝ
## ክፍያ

19. ማንኛውም አመልካች ለማመልከቻ ማስገቢያ የማይመለስ ብር 50.00 መክፈል አለበት፣

20. አመልካቾች የሙያ ብቃት የምስክር ወረቅት ለማግኘት ብር 300.00 መክፈል አለባቸው፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

21. የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ለማሳደስ አመልካቾች ለእያንዳንዱ ዕድሳት ብር 100.00 መክፈል አለባቸው::

## ክፍል አሥር
## የሙያ ብቃት ማስረጃን ስለማሻሻል እና የማማከር አገልግሎት ሥራን ስለማቋረጥ

22. ባለሙያን ስለመልቀቅ

22.1 ድርጅቱ ካቀረባቸው ባለሙያዎች ውስጥ ማናቸውም ባለሙያ የማማከር አገልግሎት ሥራውን ሲለቅ ድርጅቱ ይህንኑ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት በቅድሚያ ለገምጋሚው አካል አሳውቆ ሌላ ተተኪ ባለሙያ ከቅጥር ውል እና በዚህ መመሪያ መሠረት አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች ሰነዶች ጋር ማቅረብ ይኖርበታል::

22.2 ገምጋሚው አካልም የቀረበውን ባለሙያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ገምግሞ ከለቀቀው ባለሙያ ጋር ቢያንስ ተመጣጣኝ ሆኖ ሲያገኘው አስፈላጊው መሟላቱን አረጋግጦ ማሻሻያውን ይቀበለዋል::

22.3 ሆኖም ግን ድርጅቱ ተተኪ ባለሙያ ካላቀረበ ወይም ተተኪ ይሆናል ብሎ ያቀረበው ባለሙያ ከለቀቀው ባለሙያ ጋር በሙያ ዓይነትና ደረጃ ተመጣጣኝ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ተተኪ ይሆናል ተብሎ የቀረበው ባለሙያ በዚህ መመሪያ መሠረት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ወይም ድርጅቱ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዚህ መመሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አሟልቶ ማቅረብ ካልቻለ ገምጋሚው አካል ይህንኑ ለድርጅቱ በጽሑፍ ካሳወቀ በኋላ ድርጅቱ በሃያ (20) ቀናት ውስጥ ተመጣጣኝና ብቁ የሆነ ባለሙያ ከተሟላ ሰነድ ጋር ካላቀረበ ገምጋሚው አካል በለቀቀው ባለሙያ ሙያ ላይ በመመርኮዝ የድርጅቱን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ያሻሽለዋል::

23. አዲስ ባለሙያን ስለመጨመር

የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማስረጃ የተሰጠው ድርጅት በዚህ መመመሪያ መሠረት ለማማከር አገልግሎት ብቁ የሆኑ ተጨማሪ ባለሙያዎችን ቀጥሮ ለገምጋሚው አካል ሊያቀርብ ይችላል:: ገምጋሚው አካልም የቀረቡት ባለሙያዎች በዚህ መመመሪያ መሠረት ብቁ ሆነው ሲገኙ በባለሙያዎቹ ሙያ ላይ በመመርኮዝ በሌሎች ተጨማሪ ዘርፎች የብቃት ማስረጃ ለድርጅቱ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል::

24. የማማከር አገልግሎት ሥራን ስለማቋረጥ

የማማከር አገልግሎት ባለፈቃድ የማማከር አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ወዲያውኑ ለገምጋሚው አካል በማሳወቅ የወሰደውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መመለስ አለበት::

## ክፍል አሥራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

25. በባለሙያ ቅጥር ላይ የሚደረግ ለውጥን በዚህ መመሪያ መሠረት በቅድሚያ ያላሳወቀ ድርጅት ይኸው ሁኔታ በሙያ ብቃቱ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ ለመጀመሪያ ጥፋት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ይደረጋል:: ማስጠንቀቂያው



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

ከደረሰው በኋላ ተመሳሳይ ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የሙያ ብቃት ማስረጃው ይወሰድበታል::

26. ከማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማስረጃ ጥያቄ፣ ማሻሻያ እና ዕድሳት ጋር በተያያዙ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንኛውም አመልካች አግባብ ባላቸው ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል::

27. በዚህ መመሪያ መሠረት በሚሰጥ የሙያ ብቃት ማስረጃ ያለአግባብ እና ከሙያው ሥነ ምግባር ውጭ የሰራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት አግባብ ባላቸው ሕጎች ተጠያቂ ይሆናል::

28. በሚሰጠው የሙያ ብቃት ማስረጃ ላይ ባልተጠቀሱ የማማከር አገልግሎት ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ መገኘት ያልተገባው የሙያ ብቃት በማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ እንደመሠማራት ተቆጥሮ በሕግ ይጠየቃል::

29. የሙያ ብቃት ማስረጃውን በዚህ መመሪያ መሠረት አቅርቦ ያሳደሰ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ማስረጃው ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን ካበቃበት ቀን ጀምሮ የማማከር አገልግሎት ሥራውን በፈቃዱ እንደተወ ይቆጠራል::

30. የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት የጠፋበት ሰው አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች መሠረት የምስክር ወረቀቱ የጠፋበት መሆኑን አረጋግጦ ሲቀርብ ብር 300.00 ( ሶስት መቶ ብር)በማስከፈል ሌላ ተመሳሳይ የምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል::

## ክፍል አሥራ ሁለት

## መመሪያውን ስለማስፈፀም

31. የማዕድን ሥራዎች መምሪያ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም አስፈላጊው ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል::

## ክፍል አሥራ ሦስት

## መመሪያው የሚፀናበት ቀን

32. ይህ መመሪያ ከዛሬ ነሐሴ 8 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum